**14 ኛ ዓመት ቁጥር 1**
**14th Year No 1**

ባህር ዳር ጥር **26** ቀን **2001** ዓ.ም
**Bahir Dar 27th, February 2.2009**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር **159/2001** ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአማራ ክልል ሕዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ማስተላለፊያና መረከቢያ የመግባቢያ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ

## in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ
መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት
የወጣ

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 3.95
Unit price ------

### አዋጅ ቁጥር **159/2001** ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአመራ ክልል ሕዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ማስተላለፊያና መረከቢያ የመግባቢያ ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የሰማዕታት ህውልት የአማራ ክልል ህዝቦች የህዝባዊ ተጋድሎና መራራ ትግል ፅናት መገለጫ ህያው ምስክር ሆኖ ተቋማዊ መልክ ይዞ መቀጠል እንዳለበት ስለታመነበት፣

## አዋጅ ቁጥር 159/2001 ዓ.ም

ሐውልቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካትና የሰማዕታትን አደራ ወደፊት በማራመድ ቀጣይነት ያለው ተቋም እንዲሆን ለማስቻል በክልሉ መንግሥት ባለቤትነት ቢተዳደር ጠቀሜታው የላቀ በመሆኑ፣

ይህንን ዓላማ ዕውን ለማድረግ በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 11 ክልል ውስጥ የሚገኘው የአማራ ሰማዕታት ሀውልትና በሥሩ የሚገኙ የተለያዩ ንብረቶችና ዶክመንቶች፤ ቤተ መጽሐፍት፤ እንዲሁም የመዝናኛ ቦታ ዓላማውን በጠበቀ መንገድ እንዲያስተዳድረው ለክልሉ መንግስት እንዲተላለፍ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና በብሔረ- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እንዲተላለፍ በብሔረ- አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ/ ብአዴን/ መካከል በባህር ዳር ከተማ È ጉሜ 3 ቀን 2000 ዓ.ም የርክክብ ስምምነት በመፈረሙ፣

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀፅ 3/1/ ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ“ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአማራ ክልል ሕዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ማስተላለፊያና መረከቢያ የመግባቢያ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር 159/2001 ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. የመግባቢያ ስምምነቱ ስለመፅደቁ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና በብሔረ- አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ብኢ.ዴን/መካከል በባህር ዳር ከተማ የተፈረመው የአማራ ሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ማስተላለፊያ መረከቢያ የመግባቢያ ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**3.** ስለሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ሥልጣን

በስምምነቱ የተካተቱትን ጉዳዮች የሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት በየሥራ ሀላፊነታቸው ስምምነቱ በተሟላ ሁኔታ ሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሀላፊነት በዚህ አዋጅ መሠረት ተስጥቷቸዋል።

**1.** አወጁ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ - ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀመሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ጥር **16** ቀን **2001** ዓ.ም

አያሌው ጎበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ፕሬዚዳንት